“ለሀገራችን ጥቅም መቆም ብቻ ከሆነ በእኛና በኢህአዴግ መካከል ያለዉ ልዩነት በቀላሉ ሊፈታ ሚችል ነዉ” በሚል ርእስ ዶ/ር ያእቆብ ሀ/ማርያም ለኢትዮጵያ ህዝብና ክቡራን ዳኞች የፃፉትን ግልፅ ደብዳቤ ሳነብ አንድ ጥያቄ ለራሴ ጠይቄ አእምሮዬን ሊያሳርፍ የሚችል መልስ ለራሴ ሰጠሁት።

ጥያቄዉም ሰዎች የሚፈፅሙትን ተግባር ለምን ይፈፅማሉ ወይንም what motivates people to do what they are doing? የሚል ነበር።

ለጥያቄዬ መልስ ለማግኘት ብዙም አልቸገረኝም። ምክንያቱም እንደአቅሜም ቢሆን የ ማኔጅመንት ኮርስ ወስጄ ስለነበር የተለያዩ የሞቲቬሽን ንድፈ ሀሳቦች ወይንም ቲዎሪዎችን መከለሱ በቂ ነበር።

ብዙ የሞቲቬሽን ቲዎሪዎች ቢኖሩም ዶ/ር ያእቆብ ወደፖለቲካዉ አለም ለምን እንደገቡ ከሰጡት ትንታኔ ጋር ተዛማጅነት ያለዉን የ ማስሎብን ንድፈ ሀሳብ (A.MaSlov’s hierarchy of needs theory)ን ማየቱ ተገቢ ነዉ።

ዶ/ር ያእቆብ እንዳሉት በቅንጅት ዙሪያ የተከሰሱትና ዛሬ በተከሳሽነት የቀረቡት ግለሰቦች፡ በተለይም አዛዉንቶቹ፡ ፓርቲ ዉስጥ የገቡት በአፍሪካ በሰፊዉ እንደሚደረገዉ ስልጣንን ተገን አድርገዉ ገንዘብና ሌሎች የግል ጥቅማቸዉን ለማሳደድ አልነበረም። የስልጣን ፍጎትም አልነበራቸዉም።

የኔም ጥያቄ በርግጥ ለምን የሚል ነበር።

እንደማስሎብ ከሆነ ሰዎች የተለያዩ ፍላጎቶች አሏቸዉ። ከፍላጎቶቻቸዉ ዉስጥ የመጀመሪያዉን እና አብዛኛዉን ደረጃ የሚይዙት (Basic Physiologic needs) ወይንም መሰረታዊ የሆኑ የሰዉ ልጅ ፍላጎቶች፤ማለትም መጠለያ፡ምግብ፡ልብስና የመሳሰሉት ናቸዉ።

ማስሎብ በመቀጠልም የሰዉ ልጅ ፍላጎት ማለቂያ እንደሌለዉ በመግለፅ አንዴ መሰረታዊ ፍላጎቱን ያሟላ ሰዉ በመቀጠል የተለያዩ (need hierarchies) የፍላጎት እርከኖችን፡ ማለትም (Safety needs ወይንም የደሕንነት ፍላጎት: from the elements and enemies, Love needs የመፈቀር ፍላጎት: desire for love, affection, and belonging, Esteem needs የማንነ/ዋጋ ያለዉ ሰዉ የመሆን ፍላጎት: self-perception as a worthwhile person.) ዕያለፈ በመጨረሻም Self-actualization need ወይንም ራስን እዉን የማድረግ ፍላጎት: becoming all that one can become ላይ ይደርሳል።

"የሰዉ ልጆችም በየእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸዉ የሚከዉኑት ተግባር (ፖለቲካንም ጨምሮ) በመጀመሪያ የሚያስፈልጋቸዉን የ ፊዚዎሎጂክ ኒድ ለማሟላት ነዉ በመቀጠልም በየደረጃዉ ያሉትን ፍላጎቶቹን ለማሟላት ነዉ።"

ዶ/ር ያእቆብ እንደነገሩንና ሁላችንም እንደምናዉቀዉ እርግጥ ነዉ በቅንጅት ዙሪያ የተሰባሰቡት የፓርቲ አባላት የመጀመሪያዎቹ አራት ፍላጎቶች ተሟልተዉላቸዋል ። ምክንያቱም በቂ የሆነ ምግብና መጠለያ ትዳር ደህንነትና የማንነት ፍላጎት/ስራ አሏቸዉ። ስለሆነም እርሳቸዉ እንዳሉት እነኚህ ፍላጎቶች ወደፖለቲካዉ አያስገቧቸዉም።

እንደ ማስሎብ ከሆነ የሚጎድላቸዉ ፍላጎት ቢኖር የመጨሻዉ ፍላጎት ይመስለኛል።

በአዚህም መሰረት እርሳቸዉ እንዳሉትና ሌሎች የቅንጅ አመራሮች ሁል ጊዜ ሲናገሩ እንደምኒሰማዉ ወደፖለቲካዉ የገቡት ተራ የሆነ የግል ጥቅም ለማሳደድ ሳይሆን ለሀገራቸዉ ሰላምና ዴሞክራሲ የበኩላቸዉን ለማበርከት ነዉ። በሌላ አነጋገርም የመጨረሻዉን ፍላጎት (self actualization need) እዉን ለማድረግ።

በእኔ እምነት ስህተት የሰሩት ደግሞ ያኔ ነዉ፡፡

እንደማስሎብ ከሆነ self actualization need ን እዉን ማድረግ ማለት becoming all that one can become ወይንም መሆን የምትችለዉን መሆን ማለት ነዉ፡፡ ይህ ሲባል ግን መሆን የማይገባህን ሁን ማለት አይደለም፡፡

መሪነት(leadership) ፡ሲያዉም የሀገር/ፖለቲካ፡ self actualization need ን ከማሟላት የዘለለ የዉስጥ ጥንካሬ፡ ሀገራዊ ራእይንና የአላማ ፅናትን ይጠይቃል፡፡

የምትችለዉን መሆን ማለት የግድ የፖለቲካ ስልጣን መያዝን ወይንም የካቢኔ አባል መሆንን አይጠይቅም፡፡

ለሀገር ልማትና ዴሞክራሲ አሥተዋፅኦ ለማበርከት የምትችለዉን መሆን ማለት የግድ የህግ አዉጪ አካል ሆኖ ህጎች ላይ መፈረምንም አይጠይቅም፡፡

በሀገር ልማት ሁሉም በሙያዉ አስተዋፅ በማበርከት መሆን የሚቻለዉን መሆን ግን ይቻላል፡፡ ዕረኛዉ የተዋጣለት እረኛ በመሆንና ጠበቃዉም በመክሊቱና በተሰጥኦዉ የተዋጣለት ጠበቃ በመሆን፡፡

ከዚህ ዉጭ አልፎ self actualization need ን ለማሟላት የግድ የፖለቲካ ስልጣን መያዝ አለብኝ ማለት ግን የፍላጎቶች መዛባት ወይንም መጣረስን need fallacy/paradox ን ስለሚያመጣ ለሀገር ልማትና ዴሞክራሲ አስተዋፅኦ ከማበርከት በተቃራኒዉ ህግን ጥሶ አላስፈላጊ ወደሆነ ቅጣት ያርሳልና አርቆ ማሰብን ይጠይቃል፡፡

አላዋቂ ሳሚ ምን ይለቀልቃል እንዲሉ፡፡ ………ዳ.ዘ.